ጥር ፯ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም(January 15,2018)

ይድረስ ለኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ!

## ጥሪ - ከትግሬ-ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ውድቀት በኋላ ወዴት?

ወያኔ እንዴት ይወድቃል? መቼ ይወድቃል? የሚሉት የሕዝባችን የ27 ዓመታት መሠረታዊ ጥያቄዎች ሆነው የዘለቁ መሆናቸው ይታወቃል። የመውደቂያ ቀኑ ይህ ነው ተብሎ በግልጽ ተለይቶ አይታወቅ እንጂ፣ የትግሬ ወያኔ አገዛዝ እንደማንኛውም አምባገነን አገዛዝ በሕዝብ አመጽ መውደቁ የማይቀር እንደሆነ ከታሪክና ከኅብረተሰብ ዕድገት ተመክሮ የሚታወቅ ነው። የአወዳደቁ ሁኔታም አገዛዙ በሕዝቡ ላይ በሚያደርሰው በደልና ግፍ የሚፈጥረው የሕዝብ ምሬትና ቁጣ፣ ከተናጠል ወደ ተደራጀ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ መለወጥ የሚያስከትለው ግፊት እንደሆነ ይታመናል። ከዚህ አንፃር፣ የትግሬ-ወያኔን አገዛዝ ለመጣል ሕዝባችን በተናጠል መታገል የጀመረው ገና ከወያኔ ጽንሰት ጀምሮ ቢሆንም፣ የተቃውሞ እንቅስቃሴው ከግለሰብ ወደ ማኅበረሰብ ለማሸጋገር ጊዜ በመፍጀቱ፣ ኢትዮጵያዊው ዜጋ አምረው በሚጠሉት የፋሽስት ጣሊያን ባንዳ ልጆች፣ የትግሬ-ወያኔ አናሳ ቡድን ለ27 ዓመታት፣ ለያይተውና ከፋፍለው፣ አጥፊና ጠፊ አድርገው አቧድነው፣ የዜግነት መብትና ጥቅሙን አሳጥተው እንዲገዙት ዕድል የሰጠ መሆኑን ያለፈባቸው የመከራ ዓመታት ያሳያሉ።

ያም ሆኖ፣ የግፉ ጽዋ ሞልቶ መፍሰስ በመጀመሩ፣ ሕዝባችን ላለፉት 3 ተከታታይ ዓመታት እንደሕዝብ ከመሃል እስከ ዳር፣ ከከተማ እስከ ገጠር ያለው በአንድ ድምፅ፣ «ወያኔ ይወገድ!»፣«የትግሬ-ወያኔ ዘረኛና ከፋፋይ አገዛዝ ይብቃ!» በማለት ከአፋኙና ገዳዩ የአጋዚ ሠራዊት አፈሙዝ ፊት በመቆም የተቃውሞ ድምፁን የሕይወት ዋጋ እየከፈለ ማሰማቱን በስፋት በመቀጠሉ፣ የአናሳዎቹ ቡድን አገዛዝ እንደድሮው አስፈራርቶና አስገድዶ ለመግዛት ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ከሚያወጣቸው መግለጫዎችና በሕዝቡ የተቃውሞ መጠን መሥፋት በግልጽ እየተስተዋለ ነው። ይህም ወያኔ መቼ ይወድቃል? የሚለው የጊዜ ጥያቄ አሁን! ወይም ዛሬ የሚሉ መልሶችን በማያሻማ ሁኔታ እያረጋገጠ እንደሚገኝ አገሪቱና ሕዝቡ የሚገኙበት ነባራዊ ሁኔታ ያሳይል። የአወዳደቁ ሁኔታም በተባበረ ሕዝብ ትግል እንደሆነ በተጨባጭ እየታየ ነው።

ዛሬ የአገራችንና የሕዝባችን መሠረታዊ ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ወያኔ መቼና እንዴት ይወድቃል የሚለው ሳይሆን፣ ***ከወያኔ ውድቀት በኋላ ምን ይከተላል? ምንስ ይመጣል?*** ዘረኛው የትግሬ-ወያኔ ቡድን «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብለቀል» እንዳለችው እንስሳ፣ ወይም እኔ በሥልጣን ላይ ከሌለሁ ሁሉም ነገር ይጥፋ በሚል የአምባገነኖች እሳቤ የሚመራው ዘረኛ ቡድን በመጨረሻ የሕቅታ መፈራገጥ ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ቀንሶ፣ የሥልጣን ሽግግር ክፍተት ሳይኖር፣ የአገሪቱንና የሕዝቡን ሰላምና አንድነት አረጋግጦ ወደ በሕግ የበላይነት የሚመራ ዲሞክራሲዊ ሥርዓት ለመግባት የሚያስችል፣ ከወያኔ ውድቀት በኋላ ምን ዓይነት አስተዳደር ይመጣ ይሆን? የሚለው የብዙ ቅንና ዕውነተኛ ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል።

ጥያቄው ደግሞ ጊዜ የሚሰጠው ሳይሆን፣ አጣዳፊና ሁሉንም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖችን በሙሉ ያሳተፈ፣ ከግለሰብና ከቡድኖች ፍላጎት በላይ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ብሔራዊ ጥቅም፣ የሕዝቡን አንድነትና ዕኩልነት በግልጽ ሊያስጠብቅና ሊያረጋግጥ የሚችል ራዕይ የሰነቀ መልስ ይሻል። ለዚህ ጥያቄም የተለያዩ ወገኖች የመሰላቸውንና የታያቸውን መልሶች በየበኩላቸው የሰጡና እየሰጡም ያሉ እንደሆነ ይስተዋላል።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት እንደ ሁሉም በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል ብለው እንደሚታገሉ ድርጅቶችና ስብስቦች ሁሉ፣ ከወያኔ ውድቀት በኋላ ምን ይከተል ይሆን? ብለው ከሚጨነቁት ወገኖች አንዱ በመሆኑ፤ በሕዝባችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ኅሊናውን ጨምዶ ለያዘው ለዚህ ጥያቄ ፣ «የሽግግር ጊዜ መተዳደሪያ» ርዕስ ሥር ያሰፈረውን መልስ ለውይይት ለሕዝባችን በይፋ ያሳውቃል።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!**
**የዐማራው ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!**

**የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ)**